## ጉዞ ወደ ኤማሁስ ከጌታ ጋር

በመንገድ ሲነገረን መጻሕፍትንም ሲከፍትልንም ልባችን ይቃጠል አልነበረምን?(ሉቃ 24:32)
በዚህ አምድ በአኗኗራችን ይበልጥ ክርስቶስን መምሰል እንድንችል ቅዱስ ቃሉን በመመርኮዝ መንገዶችን የሚጠቁሙ ኃሳቦች ይስተናገዳሉ::

# ሚስጥረ ንሥሓ : የዝናብ መጥረጊያችን

በደሌን እናገራለሁና፤ ስለ ኃጢአቴም እተክዛለሁ (መዝ 38:18)

በመኪና በምንጓዝበት ጊዜ ዝናብ ሲዘንብ እይታችን እንዳይጋረድ የዝናብ መጥረጊያችንን እንጠቀማለን:: ያለበለዚያ ውጤቱ መንገድ መሳትና ለክፉ እስከ ሞት ለሚያደርስ አደጋ መጋለጥ ይሆናል:: የፊት መስታወቱ ከፀዳ በኃላም አሁንም በጉዞ ላይ እያለን መዝነቡን ከቀጠለ እኛም አጥርተን ማየት እንድንችል የዝናብ መጥረጊያችንን መጠቀም አናቆምም::

በክርስትና ሕይወት ጉዟችንም ኢየሱስ ያስተማረንን መንገድ አጥርተን እንዳናይ የተፈጥሮ ደካማነታችንን በመጠቀም አለም፤ ሥጋና ሠይጣን የኃጢአት ውርጅብኝ እያዘነቡብን ያስናክሉናል:: ወደ ከፋ ሞት አደጋም ይመሩናል:: ይህን የተቀነባበረ ሴራቸውን የምናከሽፍበት የሚወርደብንን ዶፍ የምናስወግድበት አይነተኛ መፍትሔ የዝናብ መጥረጊያችን ምሥጥረ ንስሓን በየጊዜው በአግባቡ መጠቀም ነው:: ከኦሪት ጊዜ አንስቶ በደል በፈጸምን ቁጥር መናዘዝ እንደሚገባን ተደንግጓል::[1]

በዚህች ምድር ላይ በሕይወት ዘመኑ ብዙ ኃጢአት የተሸከመ ሰው ቢኖር፤ ጅምላ ጨራሽ መሣሪያ የሠራ ወይንም የተጠቀመ፤ ብዙ እኩይ ተግባራትን የፈፀመ፤ ወይንም ራሱን ያጠፋ ሳይሆን ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ማለት ያስደፍራል:: ምክንያቱም ፍቅር አስገድዶት በወገቡ የታጠቀው ማበሻ ጨርቅ ፈቶ የኛን ኃጢአት ሁሉ ጠረገበት፤ ተሸከመው[2] "በዚያውም የመልከ ፀዲቅ ሥርዓት የዘላለም ካህን ነውና[3] ፤ ኃጢአት በዘነበብን ጊዜ የምናጠራበት የይቅርታና የስርየት ኪዳን ምስጥረ ንስሓን ተከለ::[4]

ከአምላካችን ጋር የምንታረቀው ምህረቱን በመለመን እንጂ በመደራደር አይደለም:: "አቤቱ ሕያው ሁሉ በፊትህ ፃድቅ አይደለምና ከባርያህ ጋር ወደ ፍርድ አትግባ"[5] እንደተባለው እንዲምረን እንጠይቀዋለን እንጂ እንደ ጥፋተኝነታችን ቢሆን ድሮ አልቆልን ነበር:: ነገር ግን አሁንም ነቢዩ እንደነገረን "አቤቱ ስለኛ አይደለም፤ ስለኛ አይደለም፤ ነገር ግን ስለ ስምህ ምህረትን እውነትህን"[6] እያልን እንዲምረን እንለምነዋለን::

ለእግዚአብሔር ኃጢአትን መናዘዝ ከኦሪት ጊዜ ጀምሮ የነበረ ሥርዓት መሆኑን ነህምያ ገልፆታል[7]:: ከዚያም በአዲስ ኪዳን ወልደ እግዚአብሔር አይነተኛ የደኅንነት ሚስጥር የይቅርታና የሥርየት መሣሪያ አድርጎ ተከለው::[8]

ቀናተኛ የሆነው አምላካችን ትእዛዛቱን በማይፈጽሙት ላይ ቁጣው እንደሚነድ ሁሉ፤ በዚያው መጠን መሃሪና ሩህሩህ ነው:: አንድም ነፍስ አንድትጠፋ እንደማይፈልግ ልጁ ሲያስተምረን "ከመቶዎቹ ዘጠና ዘጠኙን

*ጥቅሶች (በቅደመ ተከተል) ዘሌ 5:5፤ ዮሐ 13:3-5፤መዝ 110:4፤ ማቴ 16:19 ፤ መዝ 142:2፤ መዝ 115:1፤ ነህ 9:3፤ ዮሐ 20:23፤ ሉቃ 15:4፤ ጦቢት 13:8፤ 1ጴጥ 5:8፤ ማቴ 12:44-45 ፤ ማቴ 18:18 ፤ መዝ 36:2፤ መዝ 38:4፤ መዝ 90:8፤ ማቴ 11:28፤ዮሐ 13:29፤ማቴ 27:5፤ ማር 14:72፤ ማቴ 16:19፤ሉቃ 22:17-20፤ ሉቃ 23:40-43፤ ሕዝ 36:26፤ መዝ 51:5፤ መዝ 32:5፤ሚክ 6:6-8፤ መዝ 51:17፤ 2ቆሮ 7:8-11፤ ማቴ 22:11-13፤ 1ቆሮ 11:27፤ ሮሜ 2:5*

ባሉበት ትቶ አንዲቱን የጠፋችውን ፍለጋ እንደሚሄድና በተገኘች ጊዜ በሰማይ ቤት ታላቅ ደስታ እንደሚሆን"[9] ነው። በሌላም ቦታ "ኃጢአተኞች ሆይ ተመለሱ፣ ጽድቅን አድርጉ፣ ምናልባት ይቅር ይላችሁ ይሆናል"[10] የሚል ቃል እናገኛለን። በአካሄዳችን ምንኛ ብንጠነቀቅም ጠላታችን አጅሬ ቅዱስ ጴጥሮስ እንደሚመክረን ሊያጠቃን ሁሌም በዙሪያችን ያንጓድዳል[11]። የኃጢአት ዝናብ መጥረጊያችንን ተጠቅመን ብናፀዳውም የተጠናከረ ጦር እንደሚያዘምትብን ፤ ኢየሱስ "ልባችን ጠርገንና አፅድተን ሲያገኘን ከርሱ የከፉትን ግብረ አበሮቹን ይዞ ሊመጣ እንደሚችል[12] አስጠንቅቆናል።

አንዳንድ ጊዜ መታመኛችን እርሱ የገለፀልን እውነት ሳይሆን የራሳችን እውቀት ወይንም ማንነታችንን ሲመስለን ከአምላኬ ለመታረቅ ቄስ ምን ያደርግልኛል? ያለ "ኦኘሬተር" እራሴው እነግረዋለሁ እያለን ራሳችንን እናታልላን። ከሰማይ ሰማያት ወርዶ፣ ከድንግል ማርያም ተወልዶ ሥጋችንን ለብሶ በመካከላችን ሲኖር በሕይወቱ የሰበከውና በቃሉ ያስተማረውን ወደ ጐን ገሸሽ በማድረግ እርሱ ራሱ የተከለውን የደኅንነት ሚስጥር በቅጡ አንጠቀምበትም።

ኑዛዜ ሣጥን ውስጥ ተቀምጦ የሚጠባበቀን ካህን ከቅዱስ ጴጥሮስና ሌሎቹ የኢየሱስ ተከታዬች ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ኃጢአትን የማሠርና የመፍታት[13] ኃላፊነት ከዘር የተወረሰ ወይንም በጠመንጃ ኃይል የተጨበጠ ወይንም በገንዘብ የተገዛ ሥልጣን ሳይሆን በመቀባት የተገኘ የመንፈስ ቅዱስ ፀጋ መሆኑን እንዘነጋዋለን።

የሚስጥረ ንስሓን ሥርዓት በሚገባ ባለመረዳት አንዳንድ ጊዜ ልክ ከገበያ የምንገዛው ሸቀጥ ወይንም ልንጥለው ያዘጋጀነው ኮተት ዝርዝር ይመስል ትዝ ትዝ የሚለንን ኃጢአት ለቄሱ መዘክዘክ ብቻ አድርገን እናንኳስሰዋለን። ባንፃሩ ግን ክርስቶስ በደሙ የተከላት ቤተክርስትያን ከተቋቋመች ጊዜ አንስቶ ሁለንተናዊ የሆነ ደረጃዎች ያሉት ማለትም:- ኅሊናን የመመርመር፣ በሰራናቸው ስህተቶች ከልብ የመጸጸት፣ ዳግም አዘቅት ውስጥ እንዳንዘፈቅ በእርሱ እገዛ ቁርጥ ፈቃድ የማድረግ፣ ጥፋተኝነታችን መግለጽ (መናዘዝ) እና ተገቢውን የምስጋና መስዋዕት የማቅረብ ሥርዓት መሆኑን ባንዘነጋው ምነኛ ያማረ ነበር።

ይህንን የደህንነት ሚስጢር እርሱ ካስተማረንና የጽድቅን ጐዳና በመከተል በሕይወታቸው ከሰበኩት የቀድሞ አባቶቻችን ሕይወት ጋር በማመሳከር ብንመረምረው ይበልጥ እንድንረዳውና እንድንጠቀምበት ይረዳን ይሆናል።

አንዳንድ ጊዜ ፀጋው ሲርቀን ልባችን ሲደነድን ምንም ስህተት ያልሰራን፣ እኛ ሁልጊዜ ልክ፣ ሌሎች ሁሉ ተሳሳቱ ይመስለናል። "ኃጢአተኛ በራሱ እጅግ ይመካል። ስለዚህ ኃጢአቱ በእግዚአብሔር ፊት የሚታወቅ አይመስለውም "[14] እንደተባለው። ከእንደዚህ ካለው ውድቀት ለመዳን ሕሊናችንን እንመረምራለን። በመጀመሪያ ደረጃ ኃጢአታችን የምንነግረው ለእግዚአብሔር ሳይሆን ለራሳችን ነው። ነብዩ እንዳስገነዘበን "ኃጢአታችን ከራሳችን በላይ ከፍ ብሎ ከብዶናልና "[15] ምን ስህተት እንደፈጸምን ራሳችን እናስገንዝብ። እርሱማ ባንነግረውም ያውቀዋል። "ኃጢአታችንን በፊትህ ታኖራለህ፣ በደላችንም በሚታይ ቦታ ታስቀምጣለህ "[16] እንደተባለው ከእርሱ የተሰወረ ነገር የለም። በዚያው መጠን "ሸክማችሁ የከበዳችሁ ሁሉ ወደ እኔ ኑ"[17] ብሎ ስለጠራን፣ ወደ እርሱ እንዳንገሰግስ የሚያደናቅፈን ምን እንደሆነ እናጤናለን።

*ጥቅሶች (በቅደመ ተከተል) ዘሌ 5:5፤ ዮሐ 13:3-5፤መዝ 110:4፤ ማቴ 16:19 ፤ መዝ 142:2፤ መዝ 115:1፤ ነህ 9:3፤ ዮሐ 20:23፤ ሉቃ 15:4፤ ጦቢት 13:8፤ 1ጴጥ 5:8፤ ማቴ 12:44-45 ፤ ማቴ 18:18 ፤ መዝ 36:2፤ መዝ 38:4፤ መዝ 90:8፤ ማቴ 11:28፤ዮሐ 13:29፤ማቴ 27:5፤ ማር 14:72፤ ማቴ 16:19፤ሉቃ 22:17-20፤ ሉቃ 23:40-43፤ ሕዝ 36:26፤ መዝ 51:5፤ መዝ 32:5፤ሚክ 6:6-8፤ መዝ 51:17፤ 2ቆሮ 7:8-11፤ ማቴ 22:11-13፤ 1ቆሮ 11:27፤ ሮሜ 2:5*

ከመሳሳት የበለጠው ትልቁ ጥፋት ስህተትን አውቆ አለመጸጸትና ይቅርታ አለመጠየቅ ነው:: ከኢየሱስ የቅርብ ወዳጆች መካከል ታማኝ ነው ብሎ ገንዘብ ያዢ ያደረገው ይሁዳና[18] የተከታዮቹ ሁሉ ኃላፊ አድርጎ የሾመው ጴጥሮስ ሁለቱም ክፉ መንፈስ ተጠናውቷቸው ከድተውታል:: አንዱን ከሌላው የሚለየው በጥፋት ላይ ጥፋት እንዲሉ:- ይሁዳ በስህተቱ ተጸጽቶ የበደለውን ይቅርታ ከመጠየቅ ፋንታ ራሱን በማጥፋት የዘላለም ሞት ጽዋን ተጎነጨ[19]:: ባንፃሩ ግን ጴጥሮስ ጥፋቱን ሲረዳ ምርር ብሎ አልቅሶ በመፀፀቱና ምህረት በመጠየቁ[20] የድል አክሊል ተቀዳጀ:: የመንግሥተ ሰማያት መክፈቻንም ተረከበ::[21] አባካኙ ልጅ በጥፋቱ ተጸጽቶ ይቅርታ ለመጠየቅ ወደ ቤቱ ቢመለስ አባቱ ገና በሩቁ ሲያየው እንደራራለት ወንጌሉ ያስተምረናል[22] :: መድኃኔ አለምን ከቀረብነውና ከጠየቅነው የልባችንን መሻት እንደሚያሳካልን እሙን ነው:: አብረውት የተሰቀሉት ወንበዴች ሁለቱም እንዲያደርግላቸው የሚፈልጉትን ገለፁለት:: አንደኛው ወደ ላይ ውሰደን ሲል ሌላኛው ወደታች አውርደኝ አለው:: ለሁለቱም ምኞታቸውን ፈፀመላቸው[23]:: በአዳም ኃጢአት ምክንያት ተዘግቶ የነበረው መንግስተ ሰማይ ሲከፈት በመጀመሪያ በሩን ያለፈው ሊሞት ትንሽ ደቂቃዎች ሲቀሩት ተፀፀቶ ምህረትን የጠየቀ ነፍስ ገዳይ ወንጀለኛ መሆኑን እናስተውል::

የኃጢአት ዝናብ ውርጅብኝ የሚጠረግበትን የሚስጥረ ንስሓ በምንጠቀምበት ጊዜ ስህተቶቻችን ማወቅ፣ ጥፋተኝነታችን ማመን ተገቢ ሆኖ ሳለ፣ታጥቦ ጭቃ እንዲሉ ዳግም እንዳንሰናከል ቁርጥ ፍቃድ ማድረግ አስፈላጊ ነው:: ያንኑ ኃጢአት ደግሞ መስራት ማለት በበሽታ ተለክፍን ሐኪሙ ካደነን በኃላ መጠንቀቅ ያለብንን ነገር ችላ ብለን እንደገና በዚያው በሽታ መያዝ ማለት ነው:: ይህ እንግዲህ አዳኙን እንደመናቅ ሊቆጠር ይችላል:: በተለያዩ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታች የታደሉት የፒይትሬልቺናው ቅዱስ ፓድሬ ፒዮ ለንስሐ የሚቀርባቸውን ሰው ሲመክሩ፣ ከሰው ስህተት ከብረት ዝገት አይጠፋምና ለአሁኑ ስህተቶችህ ምህረትን ከእርሱ እንለምናለን፣ ነገር ግን እነዚህኑ ጥፋቶች ዳግም ሰርተህ እንዳትገኝ ይሉ ነበር:: ቁርጥ ፈቃዳችን የሚፀናው በኛ ኃይልና ጉልበት ሳይሆን የእርሱ ፀጋ ሲታከልበት ነው:: ነብዩ ሕዝቅያስ እንደሚነግረን "የድንጋዩን ልብ አውጥቶ የሥጋ ልብ ሲሰጠን ነው ::"[24] በእኛ ዘንድማ ያለው ደካማነት ብቻ መሆኑን ዳዊት "ገና ስፀነስ ጀምሮ በኃጥአት ነው"[25] እያለ አስረድቶናል:: ቅድስት ትሬዛ ዘሊዝየም (ትንሿ ትሬዛ) "የምስራቸው ስህተቶች ሁሉም የራሴ ሲሆኑ:- በኔ የምታዩት በጎ ነገር በሙሉ የጌታዬ ናቸው" እያለች በምትወደው ህፃን ኢየሱስ ፊት ሞገስ እንዳገኘ ች በትህትና መስክራለች::

በሚገባ ተዘጋጅተን ጥፋቶቻችንን በተቀባው ካህን አማካይነት ለፈጣሪያችን ስንናዘዝና የውስጣችንን ስንዘረግፈው፤ ስርየት እናገኛለን ብለን እንምናለን:: የ14ኛው ክፍለ ዘመን እማሆይ ጁሊያ ዘኖሪች ደጋግማ ትመክር እንደነበረው "በእግዚአብሔር ፊት ራቁታችንን መቆም" ግድ ይላል:: ቅዱስ ቃሉም የሚለን ይህንኑ ነው:: "አቤቱ ኃጢአቴን ለአንተ አስተወቅኹ፣ በደሌንም አልሸፋንኹም፣ ለእግዚአብሔር መተላለፌን እናገራለሁ::"[26]

ስህተቱን ያወቀ ፣ያመነ፣ የተፀፀተ፣ ዳግም ላለማጥፋት የወሰነ፣ ምህረት ሲጠየቅ ተገቢው ካሳ መክፈል የግድ ይኖርበታል:: የምንከፍለው ግን ከንብረታችን ላይ ሳይሆን (ቀድሞም የርሱ ነውና) ሚክያስ ነብዩ እንደሚያስተምረን "ስለ ኃጢአታችን ካሳ የሚቃጠል መሥዋዕት፣የፈሳሽዘይት ፣ወይንም የበኩር ልጅ ሳይሆን ወደ እርሱ ዘንድ በትህትና በመቅረብ ነው [27] :: ዳዊት በመዝሙሩ ይህንኑ ሲያረጋግጥልን "እግዚአብሔር ከሚቃጠል መሥዋዕት ይበልጥ የተሰበረ (የተፀፀተ) ልብ ቢቀርብለት "[28] ይመርጣል ይለናል::

*ጥቅሶች (በቅደመ ተከተል) ዘሌ 5:5፣ ዮሐ 13:3-5፣መዝ 110:4፣ ማቴ 16:19 ፣ መዝ 142:2፣ መዝ 115:1፣ ነህ 9:3፣ ዮሐ 20:23፣ ሉቃ 15:4፣ ጦቢት 13:8፣ 1ጴጥ 5:8፣ ማቴ 12:44-45 ፣ ማቴ 18:18 ፣ መዝ 36:2፣ መዝ 38:4፣ መዝ 90:8፣ ማቴ 11:28፣ዮሐ 13:29፣ማቴ 27:5፣ ማር 14:72፣ ማቴ 16:19፣ሉቃ 22:17-20፣ ሉቃ 23:40-43፣ ሕዝ 36:26፣ መዝ 51:5፣ መዝ 32:5፣ሚክ 6:6-8፣ መዝ 51:17፣ 2ቆሮ 7:8-11፣ ማቴ 22:11-13፣ 1ቆሮ 11:27፣ ሮሜ 2:5*

ቅዱስ ጳውሎስም በቆሮንቶስ ለሚገኙ ክርስቲያኖች ስላደረጉት ጥፋት ማዘን ተገቢነቱን ከዚያም መፀፀትና ንስሐ መግባት የሚያስገኛውን ጥቅም [29] ዘርዝሮ ጽፎላቸዋል፡፡ በእግዚአብሔር የመፈወስ ስጦታ የታደለቻው የቅድስት ክላራ ደናግላን ማኅበር ተከታይ እህት ብሪይዥ ማኬኔ ሚስጥረ ንስሐ የሚያስገኘው ጥቅም ስትናገር የሰራናቸውን ኃጢአቶች ከመደምሰስ ባሻገር ተመለስን ዳግም የስህተት አዘቅት ውስጥ እንድንዘፈቅ ከሚያደረግን የኃጢአት ባህል የምንታቀብበትን ጸጋ ያለብሰናል፡፡

ሚስጥረ ንስሐ በመገባት ከተዘጋጀን ዘወትር በመቅደሱ ሆኖ የሚጠባበቀን ኢየሱስን ራሱን ወደ ልባችን ማስገባት እንችላለን፡፡ ያለበለዚያ ግን የወረደብን የኃጢአት ዝናብ ሳንጠርግ ከነቆሻሻችን ወደ ቤታችን ብንጋብዘው ወይንም የርሱ ግብዣ ላይ ብንገኝ እርሱ ራሱ እንዳስገነዘበን ከሠርጉ አዳራሽ ተባረን ወደ ውጭ ወደ ጭለማ እንጣላለን ፡፡[30]

ሐዋርያው ጳውሎስም መልሶ "ሳይገባው ይህን እንጀራ የበላ ወይንም የጌታን ፅዋ የጠጣ ሁሉ እዳ አለበት"[31] ሲል እያስጠነቀቀን "ከቁጣው ለመዳን ንስሓ መግባት እንዳለብን ይመክረናል፡፡» [32]

በሚስጥረ ንስሓ አገልግሎት ከኃጢአት ባርነት ነፃ የምንወጣበት ስርዓት ከመሆኑም ባሻገር፣ ለሚያጋጥሙን እክሎችና ጭንቀቶች ጠቃሚ ምክር እና ጥበብ የምናገኝበት እንዲሁም ክፉውን እያስወገድን በጐውን የምናበለፅግበት መንገድ ነው፡፡ ምክኒያቱም ኃጢአት ሲባል ክፉ ማሰብን ፣ መናገርን፣ ማድረግን እና እንዲሁም በጎ ተግባርን (ሠናይ ምግባርን) አለመፈጸምን ያጠቃልላል፡፡ ቅዱስ ፓድሬ ፒዮ ሲያናዝዙ የሠራኸውን ስህተት ብቻ ሳይሆን መልካም ነገርም ካለ ንገረኝ ይሉ ነበር፡፡ በጐ ማድረጋችንን ማስተዋሉ ለመመፃደቅ ሳይሆን፡- የሠራነው ሠናይ ምግባር ከክፉ ሥራዎቻችንና መሥራት ከምንችለው ጋር ሲነፃፀር ትንሽ ብቻ መሆኑን ተገንዝበን የበለጠ መልካም ተግባር እንድንነሳሳ ለማበረታታት ነው፡፡

ለዚህ የደኅንነት ሚስጢር ተገቢውን ትኩረት ከሰጠነው በሕይወት ዘመናችን የተትረፈረፈ ፀጋ እንድናገኝ የሚያግዝ በመሆኑ ከበረከቱ ሁሉም ተቋዳሽ እንዲሆን ያቅማችንን ምን ማድረግ እንችላለን? ወደ ሚስጥረ ንሥሓ የምናመራው፣ በዘፈቀደ እግረ መንገዳችን ለቅዳሴ ስንሄድ ወረፋ ብዙ ከሌለ፣ ያጋጣሚ ሆኖ ቀድመን ስለደረስን፣ ወይንም ትዝ ስላለን ሳይሆን መርሐግብር ተነድፎ፣ የመሥዋዕተ ቅዳሴና የእርቅና ሥርየት አገልግሎት ክፍለ ጊዜ ተለይቶ እንደ አመቺነቱና ተግባራዊነቱ ቢቻል በየቁምስናው አለበለዚያ ጊዜ እስኪፈቅድ ድረስ በአማካይ ቦታዎች በብዙ ሀገሮች እንደሚደረገው ከሳምንት ሳምንት የሚዘልቅ የዘወትር አገልግሎት እንዲጀመር የበኩላችንን ምን ማድረግ እንችላለን?

ጉበዝ! የኃጢአት፣ የክፋት፣ የእኩይ ተግባራት ዝናብ አይሏልና መጥረጊያችንን በአግባቡ እንጠቀምበት ፡፡

## ብስራተ ገብርኤል

*ጥቅሶች (በቅደመ ተከተል) ዘሌ 5:5፣ ዮሐ 13:3-5፣መዝ 110:4፣ ማቴ 16:19 ፣ መዝ 142:2፣ መዝ 115:1፣ ነህ 9:3፣ ዮሐ 20:23፣ ሉቃ 15:4፣ ጦቢት 13:8፣ 1ጴጥ 5:8፣ ማቴ 12:44-45 ፣ ማቴ 18:18 ፣ መዝ 36:2፣ መዝ 38:4፣ መዝ 90:8፣ ማቴ 11:28፣ዮሐ 13:29፣ማቴ 27:5፣ ማር 14:72፣ ማቴ 16:19፣ሉቃ 22:17-20፣ ሉቃ 23:40-43፣ ሕዝ 36:26፣ መዝ 51:5፣ መዝ 32:5፣ሚክ 6:6-8፣ መዝ 51:17፣ 2ቆሮ 7:8-11፣ ማቴ 22:11-13፣ 1ቆሮ 11:27፣ ሮሜ 2:5*